ዕለት ግንቦት 1/ 2001 ኢኤአ

ለኢትዮጵ መጽሔትና ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ወኪል
አቶ ግርማ እንድርያስ ሙላት

በቅድምያ ሃሳቤንና ኣመለካከቴን ለኣንባቢዎቻቹህ ለማስተዋወቅ በኣምዳቹህ ላይ እድል ስለሰጣችሁኝ ኣመሰግናለሁ። ቀጥሎም ለጥያቄዎቻቹህ የሚከተሉትን መልሶች ኣቀርባለሁ፥

1 እራስዎን ከኣንባቢዎቻችን ጋር ቢያስተዋውቁን?

በቀዳማዊ ሃይለስላሴ ዩኒቨርሲቲ እስከ 3ኛ ዓመት ተምሬኣለሁ። በወቅቱ በነበረው የተማሪዎችና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ትጉህ ተሳታፊ ነበርኩ። ስለሆነም በተለያዩ ፖለቲካዊ ማህበራትና ድርጅቶች ምስረታ ላይ ተሳትፌ ኣለሁ። ደርግ ስልጣን በያዘበት ወቅትም በ1974 እኤአ ተሓህት ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ ማለትም የኣሁኑ ህወሓት መስራቾች አንዱ በመሆን ወደ ትግራይ በረሃ ወጣሁ። በትግሉ በከፍተኛ አመራር ላይ ለ12 ዓመት በተለያዩ የስራ ክፍሎች ተሳትፌኣለሁ። በ1984 እኤአ በተፈጠረው ሴራና የሃሳብ ልዩነት ድርጅቱን እንድለቅና እንድሰደድ ተገደድኩኝ። አሁን በኖርወይ የኮምፑዩተር ሳይንስ ትምህርቴን በማስተርስ ዲግሪ ኣጠናቅቄ በዚሁ መስክ እሰራለሁ። በስደትም ሆኜ በፖለቲካ ተሳትፎየን አላቋረጥኩም። መጀመሪያ ላይ በግል አሁን ደግሞ ከትዴት /የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ትብብር/ TAND (Tigrian Alliance For Democracy) ጋር በመሆን እሳተፋለሁ።

2 በ1984 እኤአ አንድ ላይ ወግነው የድርጅቱ አባል መስራች የነበራችሁትን እርስዎንና አረጋዊ በርሄን ከስልጣኑና ከድርጅቱ በማስወገድ ለስደት ያበቁዋችሁ ጉዋዶች ዛሬ እርስ በርሳቸው የሚያሻኩታቸው ምንድነው ይላሉ?

እኔንና አረጋዊን ከስልጣንና ከድርጅቱ እንድንወገድ ያደረገን መሰረታዊ ጉዳይ የሃሳብ ልዩነት አይደለም። በህወሓት የሃሳብ ልዩነትህን ይዘህ ብዙሃኑ በወሰኑት እስከተገዛህ በድርጅቱ ይሁን በሃላፊነትህ መቀጠል ማሌሊት እስኪመሰረት ድረስ የተለመደ አሰራር ነበር። ይሁን እንጂ ማሌሊት ሲመሰረት መለስ፥ አባይ፥ ስብሓትና ስዩ የስልጣን ጥማቸውን ለማርካት ሴራ በመሸረብ የነበሩትንና ያልነበሩትን ፖለቲካዊ ልዩነቶች በማንሳት በድርጅቱ ትልቅ እንቅፋት እንደፈጠሩና ድርጅቱ ለመንቀሳቀስ እንዳልቻለ አደጋ ላይ እንደሆነ በማስመሰል አቀረቡ እኔንና አረጋዊንም ከስልጣንና ከድርጅቱ እስከማባረር ሄዱ። እንደዚህ አይነት የስልጣን ጥምና ሽምያ እስካለ ድረስ በነዚህ ሴራ ሸራቢዎች እርስ በርስ መበላላት እንደሚኖር ለመገመት አያስቸግርም። ከዚህ የሴራ ቡድን ወዲያውኑ ስብሓት ተመታ። የተቀሩት ለነሱ የሚያንጨበጭቡና የሚሰግዱ አዳዲስ የአመራር አባላት እንደነ አለምሰገድ፥ ተወልደ፥ ክንፈ፥ ጫልቱ፥ ወዘተ ወደ አመራር አወጡ። ቀጥሎ አባይ ተመታ ቀጥሎም ስዩ ተመታ። መለስ አዲስ አኮብኩዋቢዎቹን ይዞ ቀረ። ነባር ታጋዮች የሚባሉትም እንደነ ገብሩ፥ አውዓሎም፥ አረጋሽ፥ ጻድቃን ደህና የሚሉትን የስልጣን ቦታ አላገኙም። ይህ ሁሉ ለመቡዋደንና ለሴራ ሸረባ የተስተካከለና የተዘጋጀ ለመሆኑ ለመገመት አያስቸግርም። አሁንም በድርጅቱ የሚታየው መሰነጣጠቅ ከዚሁ የሴራ አወጋገንና የስልጣን ሽኩቻ የመነጨ ነው።

3 ያሁኑ የህወሓት ካህናቱ ለኢትዮጵያ ህዝብ ዱብዕዳ እንደነበረው ሁሉ ለርስዎ በኖርወይ ስደትዎ ዱብዳ ነበረን?

ከላይ እንደጠቀስኩት የድርጅቱ አመራር በሴራ መቡዋደኑን ስለማቅ አንድ ቀን የአሁኑ ሁኔታ ይፈጠራል የሚል እምነት ነበረኝ። በሂደት ላይ መለስ የመጀመሪያ የሴራ አበሮቹን እየጣለ እንደሄደ ከላይ እንዳየነው ሆኖ በቡድኖቹ አሰላለፍ ላይ ግን ብዙ ያልጠበኩት ነገር አለ። አለምሰገድና ተወልደ ለመለስ ተጻራሪ ሆነው በመቆማቸው ያልጠበኩት አሰላለፍ ነው። ምናልባትም የኤሪትራው ጥያቄ አለያይትዋቸው ይሆናል።

4 ማሌሊት ሊመሰረት ሲል አባይ፥ መለስና ስብሓት ካርቱም ሄደው ነበር። በድርጅቱ ም/ሊ/መንበርነትዎ ይህንን ያውቁ ነብር፤ ከተመለሱስ በህዋላ የነበረው ሁኔታ እንዴት ነበር?

ማሌሊት ከመመስረቱ በፊት አልሄዱም። ከዛ በህዋላ ግን ተመላልሰዋል።

5 ማሌሊትን በተመለከተ የአሁኑ መለስ ዜናዊ ስለ እርስዎ ሲገልጹ 1000 ካድሬዎች ባሉበት ተከራክረው ተረተዋል ብለዋል በዕውነት ተረተዋል? ከተረቱስ እንዴት ነበር?

መረታትና አለመረታት የሚፈረደው ተቀዋሚ ሃሳቦች እኩል መድረክና ዕድል አግኝተው ውድድር ላይ ሲቀርቡ ነው። ማሌሊት ከመጣ ጀምሮ በድርጅቱ አመራሩን የሚጻረር ሃሳብ ይዞ ለመከራከር አይቻልም። እኔ ባቀረብኩዋቸው ልዩነት ሃሳቤን ለካድሬውና ለታጋዩ ለማቅረብ ጠይቄ ሃሳብህ ጉባኤ የወሰደውን አቋዋም የሚጻረር ስለሆነ ልታቀርብ አትችልም ተብየ ተከልክያለሁ። ከዚህም አልፎ ራሳቸው በጠሩት ኮንፈረንስና አጀንዳ ለመቃወም ስሞክር በተወልደ አሳሳቢነት ሃሳቤ ጉባኤ ያስቀመጠውን መስመር የሚጻረር ስለሆነ ዕድል

እንዳይሰጠኝ ከመደረጉ በላይ ከኮንፈረንሱም እንድወጣ ተደረገ። ይልቁን ይህ ኮንፈረንስ በሌላ መልኩ ለኔ ጥሩ አጋጣሚ ነበር። ድርጅቱ ተቀዋሚ ሃሳብ የማይቀበልና ጸር ዲሞክራሲ መሆኑን ለማጋለጥና በኔ ላይም ሌላ ተንኮል ፈጥረው እርምጃ ለመውሰድ እንዳይችሉ ዕድል ሰጠኝ። በዚህ ቁጭት ነበር ሃሳቦችን ለማንሸራሸር ሳይሆን እኔን ለመምታት በኮንፈረንሱ መጨርሻ ላይ ለክርክር እንድቀርብ የተደረገው። ይህን ሁኔታ ለማሳየት በወቅቱ የድርጅቱ ሊቀመንበር ከነበረው አባይ ጸሓየ ጋር የተለዋውጥኩትን ደብዳቤዎች ለመረጃ ማየት ይቻላል። ለጊዜው ግን በአጭሩ የሚከተለውን ከደብዳቤው ልጥቀስ፦

> *ከፕሮግራማችን የተለየ ሃሳብ የያዘ ጽሑፍ ይሁን ሰው በአባላችን ውስጥ ማሰራጨት አስፈላጊ ሆኖ በምናገኝበት ጊዜ እንዲሁም ጠቃሚ ሆኖ ስናገኘው ማሰራጨት አሰራራችን ስለሆነ በመብት ደርጃ ሳይሆን በጠቃሚነቱ አይተን ልዩነትህን በፓነል መልክ ከኮንፈረንስ በኋላ እንድታቀርብ ዕድል እንሰጥሃለን። /ትርጉም የራሴ/*

ለመከራከር መብት አልነበርኝም ለድርጅቱ ጠቀሜታ አለው ስለተባለ ብቻ ነበር የተፈቀደልኝ። ለምንስ በመጨርሻ ድርጅቱን አልቀበልም ካልኩኝ በኋላ ጠቃሚ ሆነ። ለድራማው ጨወታ አንድ መድረክ ብቻ መፍቀድ በቂ መሰለኝ። ከዚህም በኋላ በክርክሩ የተቀዳውን ቪድዮ እንደፈለጉት አስተካክለው ውጭ ላለው ህዝብ ለማሳየት ጀምረው ነበር። ብዙ ጥያቄና ክርክር ስላስነሳባቸው ግን ወዲያውኑ ካሴቱን ሳቡት። አሁን ካሴቱ ቢፈለግም አይገኝም። የማሌልት ኢዲሞክራሲያዊነት በስፋት ለማየት /ማሌሊት ስትጋለጥ ቁጥር 3/ በሚለው በ1987 እኤአ የጻፍኩትን ማንበብ ይቻላል።

6 አቶ መለስ ድርጅታችን ዲሞክራሲያዊ ነው ብሎአል። ትላንት የቀድሞ መሪዎችን በሰላም ወደ ስደት እንደላክነው ዛሬም ከተወገዱት ጓዶች ጋር የተፈጠረውን ችግር በድሞክራሲያዊ አግባብ በብዕርና በውይይት ፈታነው ይላሉ። ዕውነት ህወሓት ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ነበር። የዛሬውን ቀውስ በዲሞክራሲ መንገድ የመፍታት አቅም አለው ይላል?

ማሌሊት ልዩነቶችን በዲሞክራሲ መንገድ የመፍታት ልምድ የለውም። ልዩነት ሲታይ ህገውጥ የሆኑ እርምጃዎችን በመውሰድ ልዩነት የያዘውን ሰው ሃሳቡን ለማሰራጨት እኩል መድረክና ዕድል እንዳያገኝ ያረጋል፣ ሰበብ ወይም ምክንያት ፈልጎ እስር ቤት ይከትሃል። የኔንና አረጋዊን ለምሳሌ ብንመለከት ልዩነት በማሳየታችን ከአመራሩ አወረደን። ለዚሁ የተሰጠው ምክንያት ብቁ አይደሉም ነው። ይህን ያደርገው የማሌሊት ጉባኤ መርጦን በሳምንቱ ነው። ጉባኤተኛው ገና አልተበተነም ነበርና ከማእከላይ ኮሚቴ እንደወረድንም ተነገረው። ከጉባኤቶኞቹ አንድ ሁለት የሚሆኑ ጥያቄ አቀረቡ። ምርጫ ሲደረግ ሁላችሁም የማእከላይ ኮሚቴ አባሎች ግደይንና አረጋዊን ለማእክላይ ኮሚቴ አባልነት እጃችሁን በማውጣት መርጣቹኋል አሁን ምን አዲስ ነገር ተገኘ የጉባኤውንስ መብት የሚጻረር አይደለምን የሚል ጥያቄ ቀረበ። የተሰጠው መልስ ጉባኤው ተበትኗል ማእከላዊ ኮሚቴ አባሎቹን ለማውረድ መብት አለው፦ አሁን የተጠራችሁ መግለጫውን ለመስማት እንጂ ለመከራከር አይደለም በማለት ተዘጋ። እኔና አረጋዊም ለመቃወም ዕድል ተነፈገን።

ቀደም ብየ ከላይ እንደጠቀስኩት አመራሩ የማይደግፈውን ሃሳብ ጉባኤ ያጸደቀውን መስመር የሚጻረር ነው በማለት ለውይይት መድረክ አይፈቅድም። በመጨረሻም እኔን ለማሰር የተለያዩ ሰበብ ለመፍጠር ሞክሯል። አንድ ጊዜ አሰራሩን እያወቀ ሆን ብሎ በታጋዮች ቅሬታ እንዲፈጠር እያደረገ ነው የሚል ክስ ቀረበብኝ ያቀረቡት መረጃ ግን ተገልብጦ እነሱን መታቸው። ሌላ ጊዜም ቅሬታ ያላቸውን ሰዎች ለማሰባሰብ ይሞክራል የሚል ክስ ቀረበብኝ ይኸውም እንደ መጀመሪያው ብቁ መረጃ አላገኘም። በጣም አስቂኙ ግን መጨረሻ ላይ ግደይ ፖለቲካዊ መስመር የለውም፣ ፖለቲካዊ ሰውነት የለውም የሚለው ነው። አባሪ ደብዳቤዎቹን ተመልከቱ። ይህ ሁሉ የሚደረገው እኔን ሰበብ ፈልጎ ለማሰርና የታሰረውም በፖለቲካ ልዩነታችን ሳይሆን ጥፋት ፈጽሞ ነው ለማለት ነው።

ከዚህ አልፎ በመጨርሻ ጽሁፎቼን ቀምተው፣ የግል ማስታወሾቼ ተፈትሸው፣ ከአመራሩ ጋር የተለዋወጥኳቸው ደብዳቤዎች ያስመታናል የሚሉትን ቀምተው በዘበኛ ጥብቅ ጥበቃ ወደ ሱዳን እንድወጣ ተደረገ። እርግጥ በሂወት መትረፌ ዕድለኛ ነኝ። ከዚህ አልፎ የትኛውን ነው መለስ በዲሞክራሲያዊ አግባብ በብዕርና በውይይት ፈታነው የሚለው። ቶክስ አልተተኮሰም እንጂ ሂደቱ ሁሉ የአመጽና የጉልበት አሰራር ነው።

በድርጅቱ የልዩነታቸው ድምጽ ሳይሰማ ውስጥውስጡ የጠፉ የታሰሩ የተገረፉና የተጎሳቆሉ ታጋዮች ብዙ ናቸው። ተክሉ ሃዋዝ የአምራር አባል የነበረ በአረጋዊ ላይ የተወሰደውን እርምጃ አልደግፍም በማለቱ ህይወቱን አጥቷል። ህወሓት አዲስ አበባ ሲገባ የተለያዩ ጥያቄዎችን ያነሱ ካድሬዎች በብዛት እንዳሰረ የሚታወስ ነው። ለመታሰራቸው የሰጠው ምክንያት ብኩንነት ሲሆን በዚሁ የተሰጠ ህጋዊ ፍርድ የለም። አብዛኞቹ ግን ከታሰሩና ከተገረፉ በኋላ ኑሯቸውንኳ ለማሸነፍ በማይችሉበት ሁኔታና በፍራቻ ምንም ሳይተነፍሱ እንዲኖሩ አርጓቸዋል። ስም ዝርዝራቸውን አባሪ መጽሔቱን ይመልከቱ።

አሁንም ቢሆን በድርጅቱ የተፈጠረውን ቀውስ በተመሳሳይ ኢዲሞክራሲያዊ መንገድ እየፈታ ነው። ከድርጅቱ ህገደንብ ውጭ 17 አመራር 12ቱን አባረረ። የተባረሩት አመራር ሃሳባቸውን ለካድሬውና ለህዝብ እንዳይገልጹ የፖሊስና የጸጥታ መሳርያዎቹን በመጠቀም ሁሉን ዓይነት ተጽዕኖ በማድረግ ላይ ነው። ቆየት ብሎም የተለያዩ ሰበቦችን በማምጣት ማሰርና ማሳደድ እንድሚጀምር አልጠራጠርም።

በኛ ላይ የተወሰደው እርምጃና የአሁኑ አንድ ነው። ምንም የዲምክራሲ ሽታ የለውም። የተከሰቱበት ሁኔታ ግን ልዩነት አለው። አንደኛ በኛ ጊዜ ሁለት ብቻ ነበርን አሁን ግን 12 ናቸው። መለስ እነዚህን ለመጋፋት በቀላሉ የሚደረግ ሂደት አይሆንም። ሁለተኛ እኛ በበረሃ ነበርን ልዩነቱ በድርጅቱ ውስጥ ብቻ ተወስኖ ነበር። አሁን ግን በህዝብ መሃል ናቸው ልዩነቱና አካሄዱ ከህዝብ ሊደበቅ አይችልም። ሦሥተኛ በኛ ጊዜ የኦዲት ኮሚቴው እኛን በመቃወም ከአመራሩ ጋር አበረ አሁን ግን የኦዲት ኮሚቴው እነመለስን አልደገፈም።

7 እርስዎ የድርጅቱ የመረጃ / የመታወቂያ ክፍል ኃላፊ ሆነው በሚሰሩበት ወቅት የዛሬው ጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ የርስዎ የበታች ሰራተኛ ነበር ተብሎአልና መለስ እንደ ሰራተኛ እንዴት ይገመግሙታል እንደ አንድ የሃገሪቱ ጠ/ሚኒስትርነትስ ግለባህሪውስ?

በዚህ በተባለው ክፍል አልሰራሁም። መለስ ወደ አመራር ከመምጣቱ በፊትም ሆነ ከመጣ በኋላ እኔ የበላይነት ስልጣንና ሃላፊነት ስለነበረኝ የመለስንም ስራ እከታተል ነበር። መለስ በአብዛኛው የሰራው በፖልቲካ ክፍል ነው። በተለያዩ ወቅቶች ጥሩ አስትዋጽኦ ነበረው። በመጨረሻ ግን በስራው ምክንያት ያገኘውን ከካድሬዎች ጋር የመገናኘት ዕድል ሴራ ለመሸረብና ለግል ጥቅም ተጠቅሞበታል።

መለስ የመናገርና ነገሮችን በሽምደዳ የማጥናት ችሎታ አለው። ይኸም ቢሆን ከብዙ ድክመቶች ጋር ነው። ከአፉ የሚወጡትን ቃላት አይቆጣጠርም። ዘላፊ ነው። ሁሉን አውቃለሁ ባይ ነው ሌላውን ይንቃል ተራ የጹርየ አነጋገርን ይጠቀማል። ነገሮችን ረጋ ብሎ አምዛዝኖ አያይም። ከመጽሓፍ ያነበበውን ከሁኔታዎች ጋር ሳያመዛዝን ለማተግበር ይፈልጋል ዶግማቲክ ነው።

መለስ በአቋሙ ጸንቶ የሚቆም ሰው አይደለም በየግዜው ይገለባበጣል። ድርጅታችን ፕራግማቲክ ሆኖ ገደል ገብተን ነበርን ብሎ ማስተጋባት የጀመረው እሱ ነው። እኔም የተከሰስኩት ፕራግማቲክ በመሆኔ ነው። ለዚሁም የቀረቡት መረጃዎች ከድርጅቶች ጋር የነበረን ልዩነት በግልጽ አላወጣንም ለምሳሌ ከህግሓኤ ጋር የነበረን ልዩነት የሚለውና ማርክሰ ሌሊናዊ ድርጅት መሆናችንን ለዓለም ሳናሳውቅ ደብቀን መቆየታችን የሚለው ነው። አሁንስ?

ከኤሪትራ ጦርነት በኋላ ብዙ ልዩነቶች እንደነበሩ ግን ተደብቀው እንደቆዩ ተነግሮናል። ማሌሊት የሚባለው ድርጅትና ስም ስልጣን ላይ ከመጡ ሰምተን አናውቅም ካድሬዎች መኖራቸውን ግን እናቃለን። ድሮ ፕራግማቲክ ተብሎ የተኮነነውና ከራሴ ጀምሮ ሌሎች ብዙ ታጋይ የተመቱበት አሁን ጠቃሚ ሆኖ ተገኝቶ ይሆን? አሁንም በቦናፓርቲዝም ስም ሲካንበት የነበርውን ዓላማ ለመቀየር እንደተዘጋጀ ገልጾልናል። ከሁሉም የሚገርመው ግን መለስ እንደዚህ ሲገለባበጥ በራሱ ላይና በድርጅቱ ትልቅ ቀውስ አለመታየቱ ነው።

መለስ ነፍሰ ወዳድ ነው። የሚቆምለት ዓላማ የለውም። በጦርነት ፈሪ ነው ጓደኞቹን ለጠላት አጋልጦ እንደሸሸ አቃለሁ። ከበላይ ወቀሳ ከደረሰበት ሞራሉ ተሎ ይወድቃል። ከበድ ያሉ ሁኔታዎችን መቋቋም አይችልም። ምናልባትም አሁን በድርጅቱ የተከሰተው ትልቅ ቀውስ ለወደፊት የሚያሳየን ነገር ሊኖር ይችላል።

8 አቶ መለስ ድርጅቱ ታሟል ብሏል። ይህ ህመም ድርጅቱን ለሞት ያበቃዋል ወይስ ድርጅቱ አገግሞ እንደገና ትግራይንና ኢትዮጵያን ለመምራት አቅም አለው?

ድርጅቱ ታሟል ብቻ ሳይሆን በጣም ተሰነጣጥቋል። አሁን በአስተዳደራዊ እርምጃ የመለስ ቡድን የበላይነትን ይዟል። የህዝብ ድጋፍ ከትግራይም ይሁን ከሌላው ኢትዮጵያዊ የለውም። የመለስ ቡድን በስልጣን ለመቆየት በድርጅቱ የተከሰቱትን ተቃውሚ ኃይሎች ከውጭም ለሚገጥማቸው ተቃውሞ ከማንም ጊዜ በበለጠ በኃይል በማሰርና በመግደል ለማፈን ይሞክራሉ። ደርግ ወደ መጨርሻው ገደማ የደረሰበት ሁኔታ ይመስላል። ድርጅቱ ኢትዮጵያን የመምራት አቅም የለውም ድሮም አልነበረውም። ሆኖም የመውደቁ ሁኔታ የሚወሰነው በውስጡ በተከሰተው ድክመት ብቻ ሳይሆን የተቀዋሚው ሃይል ትግሉን አዋህዶ ጠንካራና ብቁ ሆኖ ሲገኝም ጭምር ነው።

9 ቀውሱ የአንድ የብሔረሰብ ድርጅት ቀውስ ነው ወይስ አጠቃላይ ባለፉት 10 ዓመታት የተሞከረው የጎሣ ፖለቲካ ቀውስ ነው?

ህወሓት ጠቅላላ ኢትዮጵያን የሚያስተዳድር /የሚገዛ/ ስለሆነ በድርጅቱ የተከሰተው ቀውስ አገሪቱን በሞላ ይነካል። ለቀውሱ ጦስ ድርጅቱ የተከተለው ፖለቲካዊ መስመር፣ አሰራርና አወቃቀር ነው።

10 ሁለቱም ወገኖች አንዱ ከሌላው ይልቅ ለትግራይና ለኢትዮጵያ የተሻለ ራዕይ የነበርኝ እኔ ነኝ ይለናል ማናቸውን እንመን?

ሁለቱም አንድ ናቸው። ልዩነት ቢኖራቸው በኤሪትራው ጦርነት በተነሱት ጥያቄዎች ላይ ነው። ሁሉም በዲሞክራሲ ያላቸው አመለካከት የተዛባ ነው። የተለየ አመልካከትን ያነሳና የድርጅቱን ሂደት የተቃወመ ሁሉ

በጋራ ሲረግጡት፣ ሲያስሩት፣ ሲገርፉትና ሲገድሉት ቆይቷል። ገብሩ አስራት ጋዜጦች እንኳን ወደ ትግራይ እንዳይገቡ የከለከለ ሰው ነው። የትግራይ ህዝብ ወሬ ለመስማት ጊዜ የለውም ብሎናል። በትግራይ ውስጥ ተቃዋሚ ድርጅት እንዳይኖር አፍነው ይዘውት ቆይቷል። ትግራይ ከአንድ ድርጅት በላይ አይችልም ብለውናል። በጠቅላላ በትግራይም ይሁን በኢትዮጵያ የሚደረጉት የዲሞክራሲና የሰብኣዊ መብት ረገጣ፣ አፈና፣ ግፍና ግድያ በጋራ ሲያካሂዱት የነበረ ነው። በቡክንነት የመጠን ልዩነት ሊኖር ይችላል እንጂ ሁሉም ተጠያቂ ናቸው። የአቶ መለስ የፖኖፓርቲዝም ሃሳብም በኤሪትርያው ጥያቄ ለቀረበበት ወቀሳና ክስ ለመሸፋፈንና ለማድበስበስ እንጂ ከፖለቲካዊ ርእዮተዓለም የመነጨ አይደለም። ለኛ ከዝንጀሮ ቆንጆ ምኑ ይመራርጥዋል ነው። ሁለቱም ለኛ አንድ ናቸው። አጥፊዎች ናቸው በህግ ፊት መቅረብ ይኖርባቸዋል።
ይህን ስል ግን አንደኛው በሌላው ላይ የሚወስደውን እርምጃ ዝም ብለን ማየት አለብን ማለት አይደለም። ይህንን አጥብቀን መቃወም ይኖርብናል። ከድርጅቱ ለተባረሩት አመራር ይሁን ሌሎች ለሚባረሩ ካድሬዎች ሃሳባቸውን እንዳይገልጹና እንዳይደራጁ የሚደረጉት ጸትታዊ እርምጃዎች መቃወም አለብን። እንዲሁም ህዝብ ወደ ፓርላማ መርጦ ያስቀመጣቸውን ወኪሎች ከፓርላማ እንዲባረሩ ማድረግ ህገ መንግስቱን የሚጻረር ስለሆነ ለዲምክርሲ እቆማለሁ የሚለው ማንኛውም ሃይል እርምጃውን ማውገዝና መቃውም ይኖርበታል።

11 እርስዎ የስልጣን ሽኩቻው ከዚህ ወዴት ያመራል ይላሉ?

ከሩቅ ሆኖ በድርጅቱ ያለውን አሰላለፍ ለማወቅ ያዳግታል። ሽኩቻው ግን አወንታዊ ፖለቲካዊ አስተዋጽኦ አለው። በመጀመርያ የትግራይ ህዝብ ድርጅቴ ብሎ አቅፎት የቆየውን የቱን ያህል የበሰበሰና የጃጀ መሆኑን እንዲገነዘብ አድርጎታል ከአሁን በኋላ በጭፍን ድርጅቱን አይከተልም። ሁለትኛ የተባረሩት አመራር እንዲሁም ለወድፊት ለሚባረሩት ካድሬዎች በድርጅቱ ውስጥ ሆነው ሃሳባቸውን ለማሰራጨት ስለማይችሉ ሌላ አማርጭ ድርጅት ማቋቋም ይገደዳሉ። ከሌሎች ሃይሎች በመተባበር ጠንካራ ተወዳዳሪ ድርጅት ሊሆን ይችላል። ይህ ሂደት ለትግራይም ለጠቅላላው ኢትዮጵያም ጠቃሚ ይሆናል። ሦሥተኛው ህወሓት እንደ ድርጅት ይዳከማል ለዲሞክራሲ ለሚደረገው ትግል ደግሞ ትልቅ እርምጃ ወደፊት ነው።

12 ሽኩቻው ለጊዜው በጠ/ሚ/ መለስ የበላይነት ተደመደመ ለማለት ይቻላልን?

ከላይ እንደጠቀስኩት ይህንኑም ከሩቅ ሆኖ በትክክል ለማስቀመጥ ያስቸግራል። አሁን የምናየው ግን የነመለስ ቡድን የበላይነት መያዙን ነው።

13 ብ1967 ዓ/ም ትግራይን ነጻ ለማውጣት ወደ ደደቢት በረሃ ገባችሁ። ዛሬ እርስዎ በኦስሎ ስደት ጓዶቹ በሸዋ መሐል ሚኒሊክ ቤ/መ ናቸው። ከ26 ዓመት በፊት በረሃ የገቡለትን ዓላማ ምን ያህል ተግባራዊ ሆኗል ይላሉ?

ከ26 ዓመት በፊት የተነሱት ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ዲሞክራሲያዊ ስርዐት ይመስረት፣ የብሄሮች መብት ይጠበቅ፣ መሬት ለአራሹ ይሰጥ የሚሉ ነበሩ።

የዲሞክራሲ ስርዐት ስንል የተለያዩ ፓርቲዎችን የሚያሳትፍ ፓርላሜንታራዊ ስርዓት እንዲኖር፣ ህግ አጽዳቂ፥ ህግ አስፈጻሚና የፍትሕ አካል መዋቅሮቹ (legislative,executive,judiciary) በግልጽ ተቀምጠው እኩል መብት እንዲኖራቸው የሚያደርግና አንዱ አካል ሌላውን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሲሆን፣ የግለሰቦች ዲሞክ ራሲያዊና ሰብኣዊ መብቶችን የሚያስከብር ስርዓት ሲሆን ማለት ነው። በዚህ አኳያ ምንም ተግባራዊ እንዳልሆነ ሁላችንም የምናየው ነው።

የብሄሮች መብት ይከበር ሲባልም ብሄሮች በአገሪቱ ወሳኝ ፖለቲካዊ መድረኮችና ውሳኔዎች ለምሳተፍ እኩል መብት እንዲኖራቸውና በዘር የተመሮከሰ አድልዎ እንዲጠፋ እንዲሁም ብሄሮች የራሳቸውን ባህልና ቋንቋ ለማጎልመስ ነበር። ይህም አልሆነም። ሁሉም ነገር የሚወሰነው በህወሕት ነው። ብሄሮችን የሚያቀራርብ ሳይሆን የሚነጣጥል አሰራርና ህጎች ተደንግገዋል። ስርዓቱ ዘራዊነቱን አጉልቶ በሚያሳይ መንገድ ተዋቅሯል። ህወሓት በስልጣን ለመቆየት ብሄሮችን እርስበርስ ስያጣላቸውና ሲያፋጃቸው እናያለን። በዚሁም ነጥብ ላይ መሰረታዊ የሆኑትን ጥያቄዎች በተግባር አላዋለም።

መሬት ለአራሹ በተግባር ውሏል። ለዚሁ ደርግም አስተዋጽኦ አለው። አርሶ አደሩ መሬት ካገኘ በኋላ ግን ተገቢውን የልማት እርዳታ አልተደረገለትም። በጣም የሚያሳዝነውም ለማዳበሪያ ብድር መክፈል ያቃተውን አርሶ አደር ከኑሮው ሲያፈናቅሉትና ወደ ከተማ እየተሰደደ በልመና ሲሰማራ ማየታችን ነው።

በአጠቃላይ የተነሳንባቸው ዓላማዎች ተግባር ላይ አልዋሉም ብቻ ሳይሆን የተጠቀሱትን ዓላማዎች የሚጻረሩ ተግባራት በከፋና በተራቀቀ መልክ ሲያራምዱ ነው የምናየው።

14 ድርጅቱ ትግራይን ነጻ ከማውጣት ይልቅ ጠቅላላ ኢትዮጵያን ነጻ ለማውጣት የፈለገው ልምንድነው አንዳንዶች እንደሚሉት ለውጡ የታክቲክ ነበር ወይስ እስትራተጂካዊ አማራጭ?

በመጀመሪያ ድርጅቱ ትግራይን ነጻ ለማውጣት የሚል ዓላማ አልነበረውም። እኔ እስከማውቀው ለነጻነት እንታገል ብሎ ጽኑ እምነት ይዞ የቆመ አካል በድርጅቱ አልነበረም። በድርጅቱ ፕሮግራም ለአጭር ወቅት ለነጻነት የሚል ዝንፈት አሳይቷል። ይህም በአመራር ተወስኖ የተደረገ አልነበረም ፕሮግራሙን ለማስተካከልና ለማሳተም ሃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች የፈጸሙት ስህተት ነበር። ስለሆነም ወዲያውኑ ታርሟል በዚሁ አኳያም የተፈጠረ ልዩነትና ክርክር አልነበረም።
የድርጅቱ ዓላማ የትግራይን መብት በዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ማስከበር ካልሆነም መገንጠል የሚል ነበር። እዚህ ላይ ድርጅቱ ትግራይን ወክሎ በኢትዮጵያ በሚመሰረተው መንግስት ከሌሎች ብሄራዊና ህብረብሄራዊ ድርጅቶች ጋር ለመሳተፍ እንጂ የኢትዮጵያን ትግል ለመምራትና ለመቆጣጠር አልነበረም። ሆኖም ህወሓት ሃይሉን ካጠናከረ በኋላ በኢትዮጵያ ወሳኝ ሃይል መሆኑንና ሌላም ተፎካካሪ ሃይል አለመኖሩን ሲያቅ ስትራተጂውን ቀየረ። ከትግራይ መሪነት ወደ ኢትዮጵያ መሪነት ተሸጋገረ።
እዚህ ላይ ሊነሳ የሚችል ጥያቄ ሊኖር ይችላል። ሌሎች እኩል ተወዳዳሪ ሃይሎች ቢኖሩና ዲምክራሲያዊ ስርዓት ቢኖር ህወሓት ይሳተፍ ነበር ወይ የሚለው ነው። በበኩሌ ከድርጅቱ ዲምክራሲያዊ ልምድና አሰራር ካለመኖር አንጻር ሲታይ መገንጠልን እንደአማራጭ ሊወስድ እንደሚችል ይታየኛል።

15 ህወሓት ውስጥ ጠዋት ማታ በተሰውት ጓዶች አጥንት እየተገዘቱና እየማሉ በስልጣን የተቆየበት ድርጅት ነው ወይስ የተቆየበት። የስልጣን ምንጬ ክህዝቡ ይሁንታ ይልቅ የስውኣት የደም ዋጋ እስከታየ ድረስ ለዲሞክራሲ ተገዥነት በር እንዴት ሊከፈት ይችላል ይላሉ?

የህወሓት ካድሬ ትልቁ ችግር ይኸው ነው። አብዛኞቹ የዲሞክራሲን ስነሃሳብ የተማሩት በነመለስና በድርጅቱ ብቻ ነው። ጠለቅ ብሎ ሌላ መጽሓፍትን በማንበብና ከሌላ ህብረተሰብ አካል በውይይትም ሆነ ክርክር ያገኘው ትምህርት የለም። ጥቂት እውቀት አላቸው የሚባሉት ካድሬዎች ግማሹ በጥቅም ከመሪዎቹ ጋር ተሳስረውል ግማሾቹም ድርጅቱን የሚነካ ሃሳብ በማቅረባቸው ተመቷል። ስለሆነም ድርጅቱ ሲነካበት የሚያሳየውን ቁጣና ጭንቀት ያህል ዲሞክራሲያዊ አሰራሮችና መብቶች ሲጣሱና ሲሸርሸሩ አያሳይም። የህወሓት ካድሬ የድርጅቱ ዲሞክራሲያዊ አሰራርና ህገደንቡ ሲጣስ ድርጅቱንም የሚንደው መሆኑን በሚገባ አልተገነዘበውም ምናልባት አሁን በመሪዎቹ የታየው መፈረካከስ ዓይኑን ይከፍትለት ይሆናል የሚል ግምት አለኝ።

16 ዛሬ በህወሓት ውስጥ መለስን ደግፈውና አቅፈው የያዙት ወገኖች ባንዱ ወይም በሌላው ወገናቸው በኤሪትራዊነት የሚጠረጠሩ ግለሰቦች ናቸው የሚል ሓሜት በትግራይ ተወላጆች ዘንድ አለ። እርስዎ በትግራይ የተወለዱ ኤሪትራዊ ነዎት። ነገር ግን በታንድ አባልነትዎ ከጠ/ሚ/ር መለስ በተጻራሪነት ከቆሙት ወገን ነዎት። ይህንን እንዴት ነው ለአንባቢዎቻችን የሚያብራሩት?

በነገራችን ላይ የተወለድኩት ጎንደር ላይ ነው። በተለያዩ ቦታዎች ኖሬአለሁ። በኣብዛኛው ያደኩብት ቦታ ግን ትግራይ ነው። ወደ ጥያቄው በመመለስ አሰላለፉና የሚነሱትን ጉዳዮች ስንመለከት ድርጅቱ የቱን ያህል እንደዘቀጠ ለመገንዘብ እንችላለን። በኢትዮጵያ ዘመናዊ መንግስት ከተመሰረተ ወዲህ ለመጀመርያ ጊዜ በከፋ መልኩ ህዝብን በጎሳና በዘር በመለያየት ሲያፋጁትና ሰብኣዊ መብት የሚጥሱ እርምጃዎችን ሲወስዱ ሁላችንም ተመልክተናል። የዚሁ ነጸብራቅ በድርጅቱ መከሰቱ የሚገርም አይደለም። ስለሆነም የተዛባ አመልካከታቸው ጠልፎ እንደያዛቸው እናያለን። በብኩሌ በትውልድ ኤሪትራዊ በመሆኔ በትግራይና በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ መድረኮች ለመሳተፍና አስትዋጽኦ ለማድረግ የገታኝ ነገር የለም። ታንድም ከዚሁ የጎሳ አመለካከት ነጻ ስለሆነና ማንኛውንም ሰው ኣላማውን እስከተቀበለ የሚያቅፍ ስለሆነ አብሬ ተሰልፌአለሁ። ታንድ በዘርና በጎሳ ላይ በመመርኮስ የሚወሰዱትን ኢዲምክራሲያዊና ኢሰብኣዊ ፖሊሲዎችና ድርጊቶች /በኤሪትራም ይሁን በኢትዮጵያ ለተፈጸሙት/ በወቅቱ አውግዟል ለወድፊትም እንዲሁ ይቃወማል ያወግዛል።

17 እርስዎ ብዙ የተባለለትን ይህወሓትና የሻዕብያ ግንኙነት ከስረ መሰረቱ ያውቃሉ ከሚባሉት አንዱ ነዎት። የጦርነቱ ማክተምና የሰሞኑ የህወሓት ውስጣዊ ቀውስ የሁለቱ ድርጅቶችን የሁለት መንግስታትን የሁለቱ ህዝቦች የወደፊት ግንኙነት ወዴት የሚያመራ ይመስሎቷል?

ስለጦርነቱና የሁለቱ ድርጅቶች ግንኙነት በሚመለከት ሰፋ ያለ ጽሑፍ በ1999 እኤአ በእንግሊዝኛ አውጥቻለሁ እሱን ማንበብ ደህና ግንዛቤን ሊሰጥ ይችላል ብየ እገምታለሁ። በበኩሌ ጦርነቱ አስፈላጊ አልነበረም። ሁለት ጸረ ዲሞክራሲ የሆኑ መንግስታትና ድርጅቶች በአጉል ፉክክርና እልክ ብዙ ህዝብ ንብረትና ሃብት የጠፋበትን፣ ብዙ ህዝብ ከኑሮው የተመሳቀለበትንና የተጎሳቆለበትን ጦርነት አወረዱብን። በህዝቦች ዘንድ ይህ ነው የማይባል ጥላቻ ፈጠሩብን። በበኩሌ ጦርነቱ በህዝቡ ላይ የፈጠረው ጠባሳ ትልቅ ስለሆነ እስኪያጋግም ጊዜ ይወስድ ይሆናል ብየ እገምታለሁ። በመንግስታቱ ደርጃ ግን ሁለቱም የኢኮኖሚና የጸጥታ ጥቅማቸውን ግምት በማስገባት ግንኙነታቸውን ለማሻሻል ይጥራሉ የሚል ግምት አለኝ። ሁለቱም መንግስታት የድንበር ችግራቸውን በጦርነት ለመፍታት እንደማይችሉና የአቅማቸው ወሰን የተረዱ ይመስለኛል።

18 በአጠቃላይ ህወሓትን /ኢህኣደግን/ ከሩቅ ሆነው እንዴት ነው የሚያዩት፥ ጠንካራ የሚባልበት ጎን ይኖረው ይሆን፥ ድክመቱስ? የመተቸት ዕድሉን ቢያገኙ እንዴት ነው የሚተቹት?

ከላይ እንደጠቀስኩት ህወሓት የተነሳባቸውን ዓላማዎች ለማተግበር እንዳልቻለና ጸረ ዲሞክራሲ የሆነ መስመር እንደተከተለ ተመልክተናል። አመራሩም ሰፋ ካለ ይዘቱ እየጠበበ ወደ የኣንድ ሰው ዲክታተርነት እየተቀየረ መሆኑን ሂደቱ እያሳየን ነው። በዓላማው ይሁን እስካሁን ባሳያቸው ሂደቶች ከህዝብ ተነጥሏል። እስካሁን ሲሞካሽበት የነበረውን የነጻ ጋዜጦችና የተቃዋሚ ፓርቲዎች ህላዌ ለሽታም እንዳይታዩ እርምጃ እንደሚወስድ ግልጽ መሆን አለበት። ሰሞኑን በተማሪዎችና በነጻ ጋዜጦች እንዲሁም በፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ የወሰደው እርምጃ የወደፊት ሂደቱ ምልከት ነው። ድርጅቱ በስብሷል ደካማ ጎኑ ካልሆነ ለኢትዮጵያ ይጠቅማል የምለው ጠንካራ ጎኑ አይታየኝም።

19 ህዝብ ሊያውቀው ይገባል አልተጠቀሰም የሚሉትና የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

በመጀመሪያ ለትግራይ ህዝብና ለህወሓት ተራው አባል የማሳስበው ህይወቱንና ንብረቱን ሰውቶ እዚህ ያደረሰውን ድርጅት እንደከዳው ተገንዝቦ ሌላ አማራጭ ድርጅት እንዲፈልግና ትግሉንም ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር እንድያስተባብር ነው። ህወሓትን ከውስጥ ሆኖ ማስተካከል ነው የሚል አመለካከት ሊሰራ እንደማይችል መገንዘብ ይኖርብናል። በኔና በአረጋዊ በሌሎች ካድሬዎች አሁንም ባመራሩ ውስጥ የተፈጠረው ቀውስ አፈታቶች ላይ የምንመለከተው ህወሓትን ከውስጥ ሆኖ ለማስተካከል እንደማይቻልና መፈናፈኛ እንደሌለ ነው።

ሌላው ለኢትዮጵያ ህዝብና ተቃዋሚ ድርጅቶች የሚመለከት ነው። ህወሓት ተዳከሟል ማለት በገዛ ራሱ ወድቆ ስልጣኑን ያስረክበናል ማለት አይደለም። እንዲያውም ለሞት ሲያጥር ያለው እርግጫና ሊያደርሰው የሚችል ጉዳት ትልቅ ነው። ስለሆነም የበለጠ ትግልና ድርጅት ይጠበቅብናል። ለዚሁም የኢትዮጵያ ህዝብ የነመለስን አምባገነን መንግስት ጥሎ በምትኩ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ለመትከል የበለጠ ዝግጅትና ተሳትፎ እንዲያሳይ ለማሳሰብ እወዳለሁ። ሌላው ትልቁ ችግራችን የተቃዋሚ ድርጅቶች ብዛትና ትግላቸውን ለማስተባበር አለመቻል ነው። ተቃዋሚ ድርጅቶች ዋናውን ጠላት ከመምታት ይልቅ እርስ በርስ በመወነጃጀልና በመቃረን የሚያሳልፉት ጊዜ ይበልጣል። ይህም ህዝቡን ለማስተባበር ቀርቶ ጭራሹን ተስፋ እንዲቆርጥ አድርጎታል። ድርጅቶች ካሁን በፊት የተሞከረውን የግንባር ምስረታ ማጠናከርና ማቀላጠፍ፣ በዓላማ ሊስማሙ የሚችሉትም በውህደት መስራት ይገባቸውል። በተናጠል የሚደረግ ትግል የትም አያደርሰንም ለችግራችንም መፍትሔ አይሆንም። በዚሁ አጋጣሚ ይህን በሚመለከት ታንድ ያወጣው መግለጫ መኖሩንም ልጠቅስ እወዳለሁ።

በመጨርሻ ከላይ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች ስመልስ ሌሎች ጥያቄዎች አስነስተው ሊሆን እንደሚችሉ አልጠራጠርም። መልሶቹ አጫጭር ስለሆኑ ሙሉ ግንዛቤ ላይሰጡ ይችላሉ። በየወቅቱ የወጡ ጽሑፎች ስላሉ እነሱን ማንበብ ይረዳ ይሆናል። ከዚሁም አልፎ ግን በጥያቄና መልስም ለወድፊቱ ለማብራራት ዝግጁ ነኝ።